# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 487/2013

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሰነዶችና ማህደር ክፍል

ግንቦት 2011 ዓ.ም

# <u>መመሪያ ቁጥር 487/2013</u>

## <u>የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ</u>

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በህግ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን በተገቢው ደረጃ ለማከናወን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ምሁራንን አቅም አቀናጅቶ በመጠቀም ዘርፉ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ የሚውልበትን አግባብ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዘርፉ በሀገር ግንባታ የሚኖረውን ድርሻ ለማጎልበት ንቁ፣ ጤናማ እና ገንቢ ትውልድ በማፍራት የሀገሪቱን ሰላም፣ አንድነትና ልማት ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሙህራንን አቅም መጠቀም ተቀዳሚ የመንግስት አቅጣጫ እንደመሆኑ ዘርፉን በስትራቴጂካዊ አመራር ለመደገፍ የሚመለከታቸውን ተቋማት፣ ባለድርሻ አካላት እና የዘርፉ ባለሙያዎችን ማቀናጀት በማስፈለጉ፤

የዘርፉ ፖሊሲችና ህግጋት አፈፃፀም ላይ አስፈፃሚ አካላት ከማስፈጸም አቅም አኳይ እና የሕዝብ ፍላጎትን ከማርካት ረገድ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት በቅንጅት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ በማስፈለጉ፤

የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 30 ላይ የተጠቀሱትን ስልጣንና ተግባራት በተገቢው ደረጃ ለማከናወን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አዉጥቷል።

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ “የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር **487/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section

## 2. ትርጓሜ

1) **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

2) **"ዘርፍ"** ማለት በሚኒስቴሩ ስር የተደራጁ የባህል፣ የቱሪዝምና የስፖርት ዘርፎች ናቸው፡፡

3) **"ሚኒስትር ዴኤታ"** ማለት በሚኒስቴሩ ስራ ያሉ ዘርፎችን በበላይነት የሚመሩ ናቸው፡፡

4) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

5) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የአማካሪ ጉባኤው አወቃቀር

## 3. መቋቋም

1. የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ (ከዚህ በኋላ **"አማካሪ ጉባኤ"** እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፤ ተጠሪነቱም ለሚኒስቴሩ ሚኒስትር ይሆናል፡፡

2. አማካሪው በዘርፍ የስራ ቡድን ሲከፈል ተጠሪነቱ ለሚመለከተው ሚኒስትር ዴኤታ ይሆናል፤

## 4. ዓላማ

ዘርፉን በተገቢው ሙያዊ ብቃት ለመደገፍ አግባብነት ያላቸውን ባለሙያዎች ተሳትፎ በማጎልበት አዳዲስ ሀሳቦችን፣ እውቀቶችና አሰራሮችን በተቋም ደረጃ በማፍለቅና በማስረፅ ዘርፉ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ ልማት ድርሻውን እንዲያበረክት ማስቻል ነው፡፡

Records Section

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሚኒቴሩ እና ለሚኒስቴሩ ተጠሪ በሆኑ ተቋማትም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስለአማካሪ ጉባኤው በጠቅላላ

## 6. የአማካሪ ጉባኤው ተግባርና ኃላፊነት

አማካሪ ጉባኤው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የዘርፉን ፖሊሲዎች፣ አዳዲስ አሰራሮችን እና ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በመገምገም ተገቢውን ሙያዊ የማሻሻያ ሐሳብ ያቀርባል፤

2) የዘርፉ ፖሊሲዎች እና ህግጋት በውጤታማነት እንዲተገበሩ የሚመለከታቸው አካላትን ድርሻ ይለያል፤ ተገቢውንም አሰራር ይመክራል፤

3) ዘርፉ ለሀገር ግንባታ፣ ለልማት እና ለሰላም የሚውልበትን ስልት በመንደፍ የሚተገበርበትን አግባብ ይመክራል፤

4) የዘርፉ አስፈፃሚ አካላት የማስፈጸም አቅም እና ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም ይለያል፤ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

5) ዘርፉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የምክክርና ዉይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤

6) ዘርፉን የሚመለከቱ አዳዲስ ሀሳቦችን ያፈልቃል፤

7) የአማካሪ ጉባኤውን የስራ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል፡፡

8) አባላቱ የተሰጣቸውን የስራ ሃላፊነት በተገቢው ሁኔታ የማያከናውኑ አባላትን የስራ አፈፃፀም ገምግሞ ከአባላት እንዲሰረዙ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የመዝገብና ማህደር ክፍል

## 7. የአማካሪ ጉባኤው አባላት ብዛት

አማካሪ ጉባኤው ከአርባ አምስት ባልበለጡ አባላት የሚመሰረት ሲሆን ከየዘርፉ አስራ አምስት ግለሰቦች የሚወጣጡበት ይሆናል፤

## 8. የአማካሪ ጉባኤው አባላት መምረጫ መስፈርቶችና አሰያየም

1) የጉባኤው አባላት የሚመረጡት በየዘርፉ ከፍተኛ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ፣ መልካም ሥነ-ምግባርና ተነሳሽነት ያላቸውና ለመስራት ፍላጎት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤

2) የአማካሪ ጉባኤው አባላት በሚኒስትር ዴኤታዎቹ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፤ ከአባላቱም መካከል ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊ እንዲመረጥ ይደረጋል፤

3) ከሚኒስቴሩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለው አካል በአባልነት ሊሰየም አይችልም፤ ሆኖም ተሰይሞ ሲገኝ በሚኒስትር ዴኤታዎቹ አቅራቢነት በሚኒስትሩ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይደረጋል፤

## 9. የስራ ዘመን

የአማካሪ ጉባኤው አባላት የሥራ ዘመን ላልተወሰነ ጊዜ ይሆናል።

## 10. የአማካሪ ጉባኤው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1) የአማካሪ ጉባኤው ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ ሆኖ በሚኒስቴሩ ወይም በአንድ ሶስተኛ አባላት ጥያቄ አስቸኳይ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል።

2) ከአባላቱ ውስጥ ሁለት ሶስተኛ በስብሰባው ላይ ሲገኝ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

3) የአማካሪ ጉባኤው ውሳኔ በጋራ ወይም በተባበረ ድምፅ ይወሰናል፤ ይህ ካልተቻለ ውሳኔው በአብላጭ ድምጽ ይተላለፋል፤

4) አማካሪ ጉባኤው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል።

Records Section

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የዘርፍ የስራ ቡድኖች እንዳስፈላጊነቱ በአባላቱ ወይም በሚኒስትር ዴኤታው አነሳሽነት ሊሰበሰቡ ይችላሉ።

## 11. የአማካሪ ጉባኤው አሰራር

1) አማካሪ ጉባኤው በየዘርፉ ተደራጅተው በዚህ መመሪያ አንቀጽ አምስት የተደነገጉ ተግባራትን ያከናውናል።

2) በየዘርፍ የተደራጁት አማካሪዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባራት በማከናወን ሪፖርታቸውን ለየዘርፉ ሚኒስትር ዴኤታዎች ያቀርባሉ፤ በየዘርፍ ደረጃ ለሚያከናውኑት ተግባራት ተጠሪነት ለዘርፉ ሚኒስትር ዴኤታ ይሆናል።

3) የየዘርፍ የስራ ቡድን ስራዎችና ስብሰባዎች በተመደቡት ሰብሳቢዎች በኩል ይመራል።

## 12. የአማካሪ ጉባኤ ማስተባበሪያ

የአማካሪ ጉባኤውን ስራዎች የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና የሚደግፍ አካል በሚኒስትር ጽህፈት ቤት ስር ከዘርፍ ባለሙያዎች ተውጣጥቶ ይደራጃል፤

## 13. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት

1. አማካሪ ጉባኤውን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
2. አማካሪ ጉባኤው እንዲያተኩርባቸው የሚያስፈልጉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያመላክታል።
3. የአማካሪ ጉባኤውን ስብሰባዎች በየጊዜው እንዲካሄዱ ይደግፋል፤ የተላለፉ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እና የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዳስፈላጊነቱ በመገምገም እንዲተገበሩ ያደርጋል።
4. አማካሪ ጉባኤውን በማንኛውም ጊዜ በየስራ ቡድን ወይም በጋራ ሰብስቦ ሊያወያይ ይችላል።

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section

5. የአማካሪ ጉባኤው የውሳኔ ሀሳቦች በሚኒስቴሩ እና በተጠሪ ተቋማት እንዲፈጸሙ ያደርጋል፡፡

6. በዚህ መመሪያ አንቀፅ ስምንት ንዑስ አንቀፅ ሁለት መሰረት በአማካሪ ጉባኤ አባልነት ለተሰየሙ ግለሰቦች ይህንኑ የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡

## 14. የሚኒስትር ዴኤታዎች ኃላፊነት

1) ለዘርፉ የስራ ቡድን አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2) የዘርፉ የስራ ቡድን አባላት ለሚያቀርቡት ነጻ ሙያዊ አገልግሎት እውቅና ይሰጣል፡፡
3) የሚጨመሩ ወይም የሚሰረዙ አባላትን ከዘርፍ የስራ ቡድን ጋር በመመካከር እንዲሰየሙ ወይም እንዲሰረዙ ያደርጋል፤
4) በስራ ቡድኑ የሚቀርቡ ምክረ-ሃሳቦችን ተቋማዊ አሰራርን ተከትሎ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም ለሚኒስትሩ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

5) ከዘርፉ የስራ ቡድን ጋር በመደበኛነት ውይይት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 15. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ፣ ማንዋል እና የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡

## 16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

## 17. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበተ ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት 2011 ዓ/ም

ሂሩት ካሳው(ዶ/ር)

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

ሚኒስትር

Records Section